# በአማራ ክልል የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም መተዳደሪያ ደንብ

2006 ዓ.ም.

ባህር ዳር

መግቢያ

በአማራ ክልል ውስጥ ሰባት የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችና ቁጥራቸው በርከት ያሉ የግልና የመንግስት ኮሌጆች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለክልሉ ልማት በተናጠል የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ እንደተጠበቀ ሆኖ በፎረም በመደራጀት አቅማቸውን ይበልጥ አዋህደው ቢንቀሳቀሱ ለክልሉና ለሀገሪቱ ልማትና መልካም አስተዳደር ግንባታ የጎላ ሚና እንደሚጫወቱ በማመን በክልሉ ውስጥ ባሉ ሰባቱ ዩኒቨርሲቲዎች አነሳሽነትና ፀንሳሽነት በአማራ ክልል የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም በሚል ስያሜ ፎረም ለማቋቋም በመታሰቡ ለፎረሙ መተዳደሪያ ይሆን ዘንድ ይህ የፎረም መተዳደሪያ ደንብ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

*አንቀጽ 1፡ መቋቋም*

በአማራ ክልል የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም ህዳር 2 ቀን 2005 ዓ.ም. ተቋቁሟል ፡፡

*አንቀጽ 2፡ ስያሜ*

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የተቋቋመው ፎረም *"በአማራ ክልል የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም"* በሚል ስም የሚጠራ ይሆናል፡፡

*አንቀጽ 3፡ ዓላማ*

የፎረሙ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. የአማራ ክልል ለሚያካሂዳቸው ማናቸውም ዓይነት የእድገት ዕቅዶችና እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ በመሆን ለክልሉ ልማትና መልካም አስተዳደር ግንባታ የበኩሉን አስተዋፅዖ ማድረግ፣
2. በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ተማሪዎች ለክልሉና ለሀገሪቱ እድገት ለማምጣት እንዲችሉ በጋራ በመመካከርና ልምድ በመለዋወጥ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት፣
3. አካባቢያዊ፣ ክልላዊና ብሎም ሀገራዊ ችግሮችን ሙያዊ እገዛ በመስጠት መፍታት፣

በደረሰኝ ቁጥር 284638 ብር 35 [illegible] ተከፍሏል

በሥ/ሂ/ቁ/የፌ/በመሆኑ በመዝ/ቁ/ 033 በቀን 30/7/06 ተመዝግቦ ወጭ ሆኗል።

4. ከክልል ቢሮዎችና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በጋራም ይሁን በተናጠል ምርምር ማካሄድ፣
5. በክልሉ ውስጥ ሰፊ የማኅበረሰብ አገልግሎት መስጠት፣
6. በተመሳሳይ ሁኔታ በተለያዩ አካባቢዎች ሊተገበሩ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን መቅረፅ፣ እና
7. የጋራ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸምና ያመጡትን ለውጥ በጋራ መገምገም ናቸው፡፡

*አንቀጽ 4፡ የፎረሙ መደበኛ አድራሻ*

የፎረሙ መደበኛ አድራሻ በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር በበላይ ዘለቀ ቀበሌ ውስጥ ነው፡፡ እንዳስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ቢሮውን አስፈቅዶ ሊከፍት ይችላል፡፡

*አንቀጽ 5፡ የበጀት ዓመት*

የፎረሙ የበጀት ዓመት ከሀምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል፡፡

*አንቀጽ 6፡ ትርጉም*

1. "ፎረም" ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመው በአማራ ክልል የሚገኙ የከፍተኛ ትምህረት ተቋማት ፎረም ነው፡፡
2. "ቢሮ" ማለት የአብክመ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ ነው፡፡
3. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡
4. "አባላት" ማለት በአማራ ክልል የሚገኙ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዚደንቶች፣ ም/ፕሬዚደንቶችና የቦርድ አባላት ናቸው፡፡
5. "ሥራ አመራር ቦርድ" ማለት በአማራ ክልል የሚገኙ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዚደንቶችን በአባልነት ያቀፈ የፎረሙ የአደረጃጀት አካል ነው፡፡
6. "መሪ ተቋም" ማለት የፎረሙን ስራዎች እንዲያስፈፅም በአባል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ ተቋም ነው፡፡
7. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

በደረሰኝ ቁጥር 284638
ብር 350 በተምበር ቁጥር
ተከፍሎበታል

በመ/ዝ/ቁ/የፈ/በመሆኑ
በመዝ/ቁ/ 033 በቀን 30/7/06
ተመዝግቦ ወጭ ሆኗል።

*አንቀጽ 7፡ የፎረሙ መደበኛ አባላት*

1. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል፡፡
2. የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ማንኛውም በአማራ ክልል የሚገኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መደበኛ አባል መሆን ይችላል፡፡

   ሀ. በፎረሙ ዓላማና ግብ የሚያምን፤

   ለ. የፎረሙን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚወጡ የሥነ-ምግባር ደንቦችን የሚቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ፣

   ሐ. በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸው ክፍያዎችንና መዋጮዎችን መክፈል የሚችል፣

   መ. በህግ መብቱ ያልተገፈፈ

*አንቀጽ 8፡ የክብር አባላት/ተባባሪ አባላት*

1. የፎረሙ አባል ያልሆኑና የፎረሙን ዓላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ፤ ፎረሙ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በፎረሙ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የክብር/ተባባሪ አባል ይሆናሉ፡፡
2. የክብር አባላት በፎረሙ ውስጥ የመምረጥ፣ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡
3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም፡፡

*አንቀጽ 9፡ የአባላት መብት*

1. ሁሉም የፎረሙ አባል ተቋማት እኩል መብት አላቸው፣
2. ከፎረሙ በፈለጉ ጊዜ የመውጣት/የመሰረዝ፣

በደረሰኝ ቁጥር 284638 ብር 350 የቴምብር ቀረጥ ተከፍሎበታል
በሥ/ሂ/ቀ/የፌ/በመሆኑ በመዝ/ቁ/ 033 በቀን 30/07/06 ተመዝግቦ ወጭ ሆኗል።

3. ማንኛውም የፎረሙ መደበኛ አባል ተቋም አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በስራ አስፈጻሚ ቦርድ የመስማት መብት አላቸው፡፡

4. ማንኛውም የፎረሙ መደበኛ አባል ተቋም ተወካይ፡-

   ሀ. ለፎረሙ ዓላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም ዓይነት ስራዎች የመስራት፣

   ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለፎረሙ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣

   ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የመገኘትና ስለፎረሙ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት፣

*አንቀጽ 10፡ የአባል ተቋማት ግዴታ*

1. ማንኛውም አባል ተቋም የፎረሙን የመመዝገቢያና የአባልነት መዋጮ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰኑ ሌሎች ክፍያዎችን በወቅቱ የመክፈል፣
2. ከአባልነት ከመሰናበቱ በፊት የሚፈለግበትን ዕዳ የመክፈል፣
3. የፎረሙን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤው የሚወጡ መመሪያዎችንና ውሣኔዎችን የማክበር፣
4. የፎረሙን ዓላማና የገባቸውን ግዴታዎች የማክበር፣ የፎረሙን ንብረት የመንከባከብና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት፣
5. በፎረሙ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት፡፡

*አንቀጽ 11፡ የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች*

1. የፎረሙ መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የሚደረጉበት ጊዜና መጠን ወደፊት በጠቅላላ ጉባኤው ይወሰናል፡፡
2. በጠቅላላ ጉባኤው በሚወሰነው የጊዜ ገደብ መሰረት መዋጮውን የማይከፍል የፎረሙ መደበኛ አባል መቀጮ ይጣልበታል፡፡ የመቀጮው ሁኔታና መጠንም ወደፊት በጠቅላላ ጉባኤው ይወሰናል፡፡

በደረሰኝ ቁጥር 284638
ብር 350 የቴምብር ቀረጥ
ተከፍሎበታል

በሥ/ሂ/ቀ/የፌ/በመሆኑ
በመዝ/ቁ/ 033 በቀን 30/07/06
ተመዝግቦ ወጭ ሆኗል።

## አንቀጽ 12፡ አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎችና ውጤቱ

1. አንድ ተቋም የፎረም አባልነቱ የሚቋረጠው፣
   - ሀ/ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሠረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣
   - ለ/ ለፎረሙ ዓላማ መሣካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሣትፎ ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር እና ይኼውም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
   - ሠ/ መዋጮውን ባለመክፈሉ በጠቅላላ ጉባኤው ከአባልነቱ ሲሰናበት፣
   - መ/ ከፎረሙ አባልነት በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ፣
2. አባል ተቋማት ከፎረሙ በመሰረዛቸው ለፎረሙ የከፈሉት ገንዘብ ወይም ቁሳቁስ አይመለስላቸዉም ወይም ማካካሻ አይሰጣቸዉም፡፡

## አንቀጽ 13፡ የፎረሙ አደረጃጀት

1. ፎረሙ የሚከተሉት የአመራር አካላት ይኖሩታል፡፡
   - ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ
   - ለ. ስራ አመራር ቦርድ
   - ሐ. መሪ ተቋም
   - መ. ዋና ፀሐፊ በቅጥር የሚመደብ
   - ሠ. እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች በጠቅላላ ጉባኤው ተወስኖ የሚደራጁ አካላት ይኖሩታል፡፡
2. ፎረሙ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው፡-



በደረሰኝ ቁጥር 284638
ብር 350 ያስከፈለ የቴምብር ቀረጥ ተከፍሎበታል

በሥ/ሂ/ቀ/የፌ/በመሆኑ በመዝገብ ቁ/ 033 በቀን 30/07/06 ተመዝግቦ ወጪ ሆኗል።

አንቀጽ 14፡ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. ጠቅላላ ጉባኤው የአባል ተቋማት ቦርድ አባላትን፣ ፕረዚዳንቶችንና ምክትሎቻቸውን እንዲሁም ሶስት የተቋሙ ተማሪዎች ህብረት አባላትን የሚያካትት ሆኖ በህግና በፎረሙ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው የፎረሙ የበላይ አካል ነው፣
   ለ. የፎረሙን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣
   ሐ. የጉባኤውን ሰብሳቢ (የፎረሙን መሪ ተቋም) ይመርጣል፣
   መ. የፎረሙን መሪ ተቋም ይመርጣል የአገልግሎት ጊዜውን ሲጨርስም ይለውጣል፡፡
   ሠ. የፎረሙን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፣ ለቢሮው እንዲደርስም ያደርጋል፣
   ረ. የፎረሙን ዓመታዊ እቅድና በጀት በመመርመር ያፀድቃል፣
   ሰ. በፎረሙ የፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣
   ሸ. የፎረሙ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
   ቀ. የፎረሙ ሂሳብ በህጉ መሰረት በኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣
   በ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣
   ተ. ፎረሙ ከሌሎች ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሠጣል፣
   ቸ. በፎረሙ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ፎረሙን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል::
2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለፎረሙ ስራ አመራር ቦርድ ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል፡፡

3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

*አንቀጽ 15: የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥ*

1. ማንኛውም የጠቅላላ ጉባኤው አባል ተቋም ወኪል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል::
2. ማንኛውም የማህበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው::
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የአባል ተቋም ወኪል በስብሰባ ላይ እራሱ ተገኝቶ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል::
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሥርዓት ፍትሀዊ፣ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል::
5. ከጠቅላላው ጉባኤ የተለየ ሃሣብ ያለው የፎረሙ አባል ተቋም ወኪል የልዩነት ሀሣቡን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል::

*አንቀጽ 16: የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባራት*

ጠቅላላ ጉባዔው ከፎረሙ አባል ተቋማት ወኪሎች መካከል የሚመረጡ ሰብሳቢና የፎረሙ ቅጥር ዋና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

1. የጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ፣
   ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል፣ ከፀሀፊው ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣
   ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፣
   ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣
   መ. ጉባኤው ያፀደቃቸው ዓመታዊ የሥራ ክንውን፣ የሥራና የኦዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል፣

284638
ቁር 35D የፎምብር ቀረጥ
ተከፍሎበታል
በሥ/ሂ/ቀ/የፌ/በመሆኑ
በመዝ/ቁ/ 033 በቀን 30/07/06
ተመዝግቦ ወጭ ሆኗል።

ሠ.ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሃፊው በአጀንዳነት ያስይዛል፣

2. **ፀሐፊ**

ሀ. ከሰብሳቢው ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣

ሐ.የፎረሙ ጽ/ቤትን ሥራ ሙሉ በሙሉ ያከናውናል፡፡

***አንቀጽ 17: የጠቅላላ ጉባኤ ስብሳባ***

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ በዓመት ውስጥ ሦስት ጊዜ ይሆናል፡፡

***አንቀጽ 18: የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት***

1. ፎረሙ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጠ ሰብሳቢ (የፎረሙ መሪ ተቋም ፕሬዚደንት) ይሆናል፣
2. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣
3. የምርጫ ጊዜ በየሶስት ዓመቱ ይሆናል፡፡
4. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
5. የፎረሙ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆዎችን የተከተለ መሆን አለበት፣
6. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም፤ ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
7. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣
8. የቀድሞ ተመራጭ በምርጫ ከተሠናበቱበት ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣

9. በጠቅላላ ጉባኤው በአጀንዳነት ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

## አንቀጽ 19: የፎረሙ ስራ አመራር ቦርድ አመሠራረት፣ አደረጃጀት፣ አባልነት፣ የስራ ዘመንና ሥልጣንና ተግባራት

### 1. አመሠራረትና አደረጃጀት

ሀ. የፎረሙ ሥራ አመራር ቦርድ የሚመሰረተው በፎረሙ ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤውና ለቢሮዉ ይሆናል፤

ለ. ሰብሳቢውን ጨምሮ ስራ አመራር ቦርዱ ሰባት አባላት ይኖሩታል፣

### 2. አባልነት

የፎረሙ ሥራ አመራር ቦርድ አባላት የሚመለመሉት በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት ይሆናል፣

ሀ. የፎረሙ ጠቅላላ ጉባኤ አባል ተቋማት ፕረዚዳንት ወይም ምክትል ፕረዚዳንት መሆን፣

ለ. ለፎረሙ ተልዕኮ መሣካት የሚያግዝ ልምድ፣ ችሎታና ሙያ መኖር፣

ሐ. የፎረሙ የቦርድ አባል ሆኖ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆን፣

### 3. የስራ ዘመን

የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፣
በጠቅላላ ጉባዔው የሚቋቋምና ተጠሪነቱ ለዚሁ አካል ሆኖ የፎረሙን የእለት ተእለት ሥራ ያከናውናል፡፡

### 4. ሥልጣንና ተግባራት

የፎረሙ ስራ አመራር ቦርድ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የፎረሙን ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርትና በጀት በማዘጋጀት ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣

ለ. የፎረሙን ዓመታዊ የሥራ መርሀ ግብርና የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣

ሐ. የፎረሙን ዓላማዎች ለማስፈጸም የገቢ ምንጮችን/የገንዘብ፣ የጉልበት ወይም የማቴሪያል ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ያፈላልጋል፣

መ. የፎረሙን ፖሊሲ ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፣

ሠ. ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ስንብት፣ ደመወዝና አበል ይወስናል፡፡

ረ. በጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎች በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

ሰ. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያስወስናል፡፡

ሸ. የአባልነት ግዴታቸውን ያልተወጡ አባል ተቋማት እንዲሰረዙ ለጠቅላላ ጉባኤው የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡

ቀ. የራሱን የአሰራር ስነ ስርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

በ. አስቸኳይ የፎረሙ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚጠራበት ምክንያት ሲያጋጥም ጥሪ እንዲደረግ ይወስናል፡፡

ተ. በጠቅላላ ጉባዔው የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

*አንቀጽ 20: የሥራ አመራር ቦርድ አባላት*

1.የስራ አመራር ቦርዱ በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ ሰብሳቢ እንዲሁም 6 አባላትና አንድ ድምፅ አልባ ፀሐፊ ይኖሩታል፣

2.ሰብሳቢው

በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡

ሀ.የስራ አመራር ቦርዱን በሊቀመንበርነት ይመራል፣

ለ. ፎረሙን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡

ሐ. በፎረሙ ሥም የተከፈተውን የባንክ ሒሳብ፣ ቼኮችንና የሂሳብ ሰነዶችን ከሚመለከተው መሪ ተቋም ሂሳብ ኃላፊ ጋር በመሆን በጣምራ ይፈርማል፣

መ. ለፎረሙ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎችን ይፈቅዳል፣

ሠ. የ3 ወር፣ የ6 ወር፣ የ9 ወርና ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፡፡

ረ. በፎረሙ ሥም ደብዳቤዎችን ይፈርማል፡፡

ሰ. የመሪ ተቋሙ ሂሳብ ኃላፊና ገንዘብ ያዥ እንዲሁም ሌሎች በስሩ የሚገኙትን የመሪ ተቋሙ ሠራተኞች እያስተባበረ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የፎረሙን የዕለት ተዕለት ሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡

ሸ. የሥራ አመራር ቦርዱን በማስፈቀድ በፎረሙ ሥም ንብረት ለመግዛትና ለመሸጥ የሚያስችሉ ውሎችን ይዋዋላል፡፡

ቀ. በጠቅላላው ጉባዔው በስራ አመራር ቦርዱ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በተግባር ላይ ያውላል፡፡

በ.. ሌሎች ለሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡

### 3. ፀሐፊው

የፎረሙ ፀሐፊ በመሪ ተቋሙ በቅጥር የሚሟላ ሆኖ ቅጥር ፀሐፊ እስኪኖር ድረስ በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጥ ፀሐፊ የሚኖረው ሆኖ ተግባርና ኃላፊነቱም፡-

ሀ. ከሥራ አመራር ቦርዱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የፎረሙን የመፃፃፍ ሥራዎች ያከናውናል፣

ለ. የሥራ አመራር ቦርዱን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣

ሐ. የፎረሙን ማህተም፣ ሰነድና መዛግብት ይይዛል፣

መ. የአባልነት ማመልከቻዎችን ይቀበላል፣

በደረሰኝ ቁ 284638
ብር 350 ተከፍሏል
በመዝ/ቁ/ 033 ዘቀን 30/07/06
ተመዝግቦ ወጭ ሆኗል::

ሠ. የፎረሙን ገንዘብ በተመለከተ ከቼክ ፈራሚዎች አንዱ ይሆናል፤

ረ. ፎረሙ የሚያከናውናቸውን የማኅበረሰብ አገልግሎት፣ ምርምር፣ ወዘተ ዶኩመንት ያደርጋል፤

ሰ. በቦርዱ፣ በቦርዱ ሰብሳቢ/በመሪ ተቋሙ ፕረዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ያከናዉናል፡፡

21. *የፎረሙ መሪ ተቋም አመራረጥ፣ የአገልግሎት ዘመንና ተግባርና ኃላፊነት*

1.የመሪ ተቋሙ አመራረጥ

ሀ. የፎረሙ ጠቅላላ ጉባዔ መሪ ተቋሙን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይመርጣል፡፡

ለ. የተመረጠው ተቋም ፕሬዚዳንት የፎረሙ ጠቅላላ ጉባኤ እና የፎረሙ ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና የፎረሙ መሪ ይሆናል፡፡

2. የመሪ ተቋሙ የአገልግሎት ዘመን

ሀ. መሪ ተቋሙ ፎረሙን በመምራት የአገልግሎት ጊዜው 3 ዓመት ይሆናል፡፡

ለ. መሪ ተቋሙ እንደገና ሊመረጥ ይችላል፤ ሆኖም በተከታታይ መመረጥ የሚችለው ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ሐ. ቀጣዩ መሪ ተቋም የመጀመሪያው የአገልግሎት ዘመኑን ከመጨረሱ አንድ ወር ቀደም ብሎ በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጥ ሲሆን በቀረው አንድ ወር ጊዜም አዲሱን የአገልግሎት ዘመኑን የጨረሰው አመራር የአመራር ልምድ የሚለዋወጡበትና ክፍተት እንዳይኖር የመሸጋገሪያ ጊዜ ይሆናል፡፡

3. የመሪ ተቋሙ ተግባራትና ኃላፊነት

1. የፎረሙ መሪ ተቋም ፕሬዚደንት

ሀ. የፎረሙ መሪ ይሆናል፣

ለ. የፎረሙን ጠቅላላ ጉባኤና ስራ አመራር ቦርድ ስብሰባዎች ይመራል፤



351

ሐ. ተጠሪነቱ ለፎረሙ ጠቅላላ ጉባኤና ሥራ አአመራር ቦርድ ይሆናል፤

መ. በፎረሙ ስም የባንክ አካውንት እንዲከፈት ያደርጋል፡፡ ይህም ፕሮጀክቶች እንዲከናወኑ የሚያግዝ ገንዘብ ነው፡፡

ሠ. የጋራ ፕሮጀክቶች በሚኖሩበት ጊዜ ፎረሙን ወክሎ ኮንትራክቶችን ይፈርማል፡፡

ረ. ፕሮጀክቶች በአግባቡ መካሄዳቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡ ከፕሮጀክት መሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር በቅርብ ክትትል ያደርጋል፡፡

ሰ. ለፎረሙ ፀሐፊ ይቀጥራል፡፡

2. የመሪ ተቋሙ ሒሳብ ኃላፊና ገንዘብ ያዥ በቅደም ተከተል የፎረሙ ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዥ ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን ተግባርና ኃላፊነታቸውም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

2.1. የፎረሙ ሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የፎረሙን ገቢና ወጪ ሂሳብ በበላይነት ይቆጣጠራል::

ለ. የፎረሙ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሳብ አሠራር ደንብ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሐ. በፎረሙ ሥም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቼክና የወጪ ሰነዶች ላይ ከፎረሙ ፕሬዝዳንት/ምክትል ፕሬዝዳንት እና ፀሐፊ ጋር በጣምራ ይፈርማል፡፡

መ. የፎረሙን የሂሳብ መዛግብት በጥንቃቄ ይይዛል/እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

ሠ. የሂሳብ መዝገብ፣ ገቢና ወጭ፣ ኃብትና እዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

ረ. ፎረሙ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ በሚሰማራበት ጊዜ ለዚሁ ሥራ የሚውሉ የተለያዩ የሂሳብ መዛግብት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡

*2.2. የፎረሙ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት፣*

ሀ. የፎረሙን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፣

ለ. የተሰበሰበውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል፣ ገቢ ያደረገበትን

በደረሰኝ ቁጥር 284638
ብር 30 ቴምብር ቀረጥ ተከፍሏል
በመዝ/ቁ/ 033 በቀን 30/07/06

ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣

ሐ. ለሥራ ማስኬጃና ለማህበሩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 1,000.00(አንድ ሺ.ህ ብር) በጥሬ ገንዘብ በእጅ ሊይዝ ይችላል፡፡

መ. ከሒሳብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሒሳብ በየወሩ ያመሳክራል፣

ሠ. የፎረሙን ቼክ ይይዛል፣

ረ. በፎረሙ መሪ ተቋም ኘሬዝዳንት ወይም ፕረዚዳንቱ ሳይኖር በምክትል ፕረዚዳንቱ እና በሒሳብ ሹሙ በወጪ ሰነድ ሲታዘዝ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፡፡

## 22: የሥራ አመራር ቦርዱ የስብሰባ፣ የድምፅ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትና የአባላት የአገልግሎት ዘመን

1. የስራ አመራር ቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በአመት አራት ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በሰብሳቢው ወይም በጸሐፊው ሊጠራ ይችላል፣
3. ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባኤው ካልተሟላ ድጋሜ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በድጋሜ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤው ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምፅ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ይፀናል፣

8. የስራ አመራር ቦርድ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ ሆኖም ለፎረሙ ስራ ለሚያወጡት ወጭዎች ማካካሻ ይከፈላል፡፡

## አንቀጽ 23፡ የፎረሙ የገቢ ምንጭ

የፎረሙ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን ከእርዳታ ሰጭዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

*አንቀጽ 24፡ የፎረሙን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል*

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ¼ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል፡፡
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ወይም ፀሀፊ የጉባኤው ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሀሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ 3/4ኛ ድምጽ ሲያገኝ ነው፡፡
4. የመተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ቢሮው ያላፀደቀው እንደሆን ባልፀደቀበት ምክንያት ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይጠራል፡፡
5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በቢሮው በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

*አንቀጽ 25: ስለፎረሙ መፍረስ*

1. ፎረሙ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ፎረሙ እንዲፈርስ በ3/4ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው ፎረሙን ለማፍረስ በወሰነው ውሳኔ ላይ የማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የመንግስት አካል ሊያመለክት ይችላል፡፡

*አንቀጽ 26፡ የመተዳደሪያ ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ*

ይህ የመተዳደርያ ደንብ በቢሮ ከፀደቀበት/የፈቃድና ምዝገባ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡